የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# በልዩ ሁኔታ የሚቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎች መመሪያ ቁጥር 13/2013

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1. አውጪው ባለስልጣን

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ (1) እና በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ (1) እና (4) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### አንቀጽ 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች መመሪያ ቁጥር 13/2013"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ነው፡፡

2. **"ቦርድ"** ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡

3 **"የምርጫ ክልል"** ማለት ለምርጫ አፈፃፀም እንዲያመች እና ሕዝቡ ወኪሎቹን እንዲመርጥ በሕግ መሠረት የሀገሪቱ ግዛት ተከፋፍሎ የሚደራጅ የምርጫ አካባቢ ነው፡፡

4. **"የአካባቢው ምርጫ ክልል"** ማለት ልዩ የምርጫ ጣቢያ የተቋቋመበት አካባቢ የሚገኝበት የምርጫ ክልል ነው፡፡

5. **"የመደበኛ መኖሪያ አድራሻ የምርጫ ክልል"** ማለት በልዩ የምርጫ ጣቢያ ድምጽ የሰጡ መራጮች የሰጡት ድምጽ የሚቆጠርበት መደበኛ መኖሪያ አድራሻቸው የሚገኝበት የምርጫ ክልል ነው፡፡

6. **"ልዩ የምርጫ ጣቢያ"** ማለት ቦርዱ ከምርጫ ክልላቸው ርቀው በካምፕ የሚኖሩ ወታደሮች፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ዜጎች፣ ከመደበኛ መኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለው በጊዜያዊ መኖሪያ የሚገኙ ዜጎች በምርጫ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መራጮቹ በሚገኙበት ቦታ ወይም አካባቢ የሚያቋቁመው የምርጫ ጣቢያ ነው።

7. **"መደበኛ የመኖሪያ ቦታ"** ማለት በልዩ የምርጫ ጣቢያ የሚመዘገቡ ነዋሪዎች በጊዜያዊነት ወደሚኖሩበት የመኖሪያ አድራሻ ከመምጣታቸው በፊት በቋሚነት የሚኖሩበት ቦታ ሲሆን እንዲሁም ተፈናቃዮች ከመፈናቀላቸው በፊት በቋሚነት ይኖሩበት የነበረበት ቦታ ነው።

8. **"ተቋም"** ማለት መራጮች በሚገኙባቸው ቦታዎች በልዩ ሁኔታ የሚቋቋሙ ምርጫ ጣቢያዎች ሊቋቋሙባቸው የሚችሉ ስፍራዎች ናቸው።

9. **"የመዝገብ ሹም"** ማለት መራጮችን እንዲመዘግብ በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የሚመደብ ምርጫ አስፈጻሚ ነው።

10. የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በአዋጁ ላይ የተሰጡ ለዚህ መመሪያ አግባብነት ያላቸው ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

### አንቀጽ 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በቦርዱ ውሳኔ መሰረት በመላ አገሪቱ በሚቋቋሙ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

### አንቀጽ 5. የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በአንዱ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሌላኛውንም ጾታ ያካትታል።

### አንቀጽ 6. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ ከቋሚ የመኖሪያ አድራሻቸው ርቀው የሚኖሩ ዜጐች በሕገ መንግሥቱ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ህጎች የተረጋገጠላቸውን የመምረጥ መብት በተሟላ መልኩ ለመጠቀም እንዲችሉ ተደራሽ የሆነ አሰራር መዘርጋት ነው።

## ምዕራፍ ሁለት

## <u>የመራጮች ምዝገባ</u>

### አንቀጽ 7. የሰነዶች ስርጭትና የመራጮች ምዝገባ ቅድመ ዝግጅት

1. ቦርዱ ለልዩ ምርጫ ጣቢያ ለመራጮች ምዝገባ ሂደት የሚያገለግሉ ሰነድና ቁሳቁስ በጊዜ ለአካባቢው ምርጫ ክልል እንዲደርሱ እንዲሁም ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት ለልዩ የምርጫ ጣቢያዎች እንዲሰራጩ ማድረግ አለበት።

2. በየደረጃው ላሉ የምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች በሚሰጥ ስልጠና ውስጥ ስለ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀትና አሰራር እንዲካተት ይደረጋል፡፡
3. የልዩ ምርጫ ጣቢያ ኃላፊዋ ለመራጮች ምዝገባ፣ ለድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ ሂደት ከቦርዱ የተላኩ ሰነዶች እና ሌሎች የምርጫ ቁሳቁሶችን በጥንቃቄ ትረከባለች።
4. የምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ከቦርዱ ወደ ልዩ ምርጫ ጣቢያዎች ሲሰራጩ የአካባቢው የፀጥታ አካላት ተገቢውን የጥበቃ እገዛ ማድረግ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 8. ስለ ትብብር

በልዩ ምርጫ ጣቢያው የመምረጥ መብት ያላቸው ዜጎች የሚገኙበት ተቋም እና ልዩ ምርጫ ጣቢያው የተቋቋመበት ተቋም ልዩ ምርጫ ጣቢያዎችን የማገዝና የመተባባር ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 9. የመራጮች ምዝገባ ቦታ

1. በቦርዱ የመራጮች ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ አግባብነት ያላቸው አንቀጾች ቢኖሩም በልዩ የምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ እያንዳንዱ የልዩ ምርጫ ጣቢያ በአንድ ክልል ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የምርጫ ክልል መራጮችን እንዲመዘግብ በሚያስችለው መልኩ ይደራጃል።
2. ከፍተኛ ቁጥር የምርጫ ክልሎች ላላቸው ክልሎች ከአንድ በላይ ልዩ የምርጫ ጣቢያ ሲቋቋም በተቋቋመው ልዩ ምርጫ ጣቢያ ውስጥ የሚስተናገዱት የምርጫ ክልሎች በግልጽ መመልከት አለባቸው፡፡
3. የአዋጁ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገጉ ሌሎች ሥፍራዎችን ጨምሮ ከተቋቋመው ምርጫ ጣቢያ ውጪ በመኝታ ቤት፣ መመገቢያ ቤት፣ ትምህርት በሚሠጥባቸው ክፍሎች፣ የተቋሙ ሥራ የሚከናወንባቸው ክፍሎች ውስጥ እና በተቋሙ ውስጥ በር ለበር እየተዘዋወሩ ምዝገባ ማከናወን ክልክል ነው፡፡
4. የአዋጁ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 5 ሥር የተደነገገው ቢኖርም ወታደሮችን ለመመዝገብ በወታደራዊ ካምፕ ውስጥ ልዩ የምርጫ ጣቢያ ማቋቋም ይቻላል፡፡
5. በአንድ ክፍል ውስጥ እንደስፋቱ ሁኔታና እንደአመቺነቱ ሁለት እና ከዛ በላይ ልዩ ምርጫ ጣቢያዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡
6. በአንድ ልዩ የምርጫ ጣቢያ የሚስተናገደው መራጮች ብዛት ከ700 መብለጥ የለበትም፡፡

## አንቀጽ 10. የመራጮች ምዝገባ ቦታ በመሆን የሚያገለግሉ ቦታዎች

ትምህርት የማይሰጥባቸው ወይም የተቋሙ ሥራ የማይከናወንባቸው ቦታዎች የልዩ ምርጫ ጣቢያ ለማቋቋሚያነት የተለዩና ለምርጫ ሥራ ምቹ የሆኑ መሆን አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 11. የመራጮች ምዝገባ ዝግጅት

1. እያንዳንዱ ልዩ የምርጫ ጣቢያ በአዋጁ መሠረት የራሱ የመራጮች መዝገብ ይኖረዋል፡፡
2. የመራጮች መዝገብ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

ሀ) የመዝገቡ የፊት ሽፋን ላይ "ክልል" በሚለው ስር ተቋሙ የሚገኝበት ክልል፣ ልዩ ምርጫ ጣቢያው የሚገኝበት የምርጫ ክልል፣ እንዲሁም የልዩ ምርጫ ጣቢያው ስምና መለያ ቁጥር ብቻ የሚገልጽ ይሆናል፡፡

ለ) የመዝገቡ የውስጥ ገጾች የልዩ መራጮቹ ድምጽ በሚቆጠርባቸው ክልሎች እና የምርጫ ክልሎች መሠረት ተከፋፍለው ይዘጋጃሉ፡፡

ሐ) ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለክልል ምክር ቤቶች ምርጫ የሚደረግባቸው የምርጫ ክልሎች አንድ አይነት ለሆኑባቸው ክልሎች የመዝገቡ የውስጥ ገጾች በምርጫ ክልሎቹ ልክ ይከፋፈላሉ፡፡ በእያንዳንዱ ገጽ ራስጌ ክልሉ እና ድምጽ የሚቆጠርበት የምርጫ ክልል ይጻፋሉ፡፡ የምርጫ ጣቢያው ወረዳ እና ቀበሌ ለመሙላት በተተውት ክፍት ቦታዎች ላይ የሚጻፍ ነገር አይኖርም፡፡ ይሁን እንጂ በመራጮች መዝገብ የውስጥ ገጽ ቅጽ "አድራሻ" በሚለው ሥር ከቤት ቁጥር፣ መንደር/ጎጥ/የቦታው ልዩ መጠሪያ በተጨማሪ የመራጩ የመደበኛ አድራሻው ወረዳ እና ቀበሌ ይመዘገባል፡፡

መ) ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለክልል ምክር ቤቶች ምርጫ የሚደረግባቸው የምርጫ ክልሎች አንድ አይነት ላልሆኑባቸው ክልሎች የመዝገቡ የውስጥ ገጾች በምርጫ ክልሎቹ ልክ ከመከፋፈላቸው በተጨማሪ ለየምርጫ ክልሉ የተመደበው ገጽ በወረዳዎች ይከፋፈላል። በእያንዳንዱ ገጽ ራስጌ ክልሉ፣ ድምጽ የሚቆጠርበት የምርጫ ክልል እና ወረዳው ይጻፋሉ። ቀበሌ ለመሙላት በተተውት ክፍት ቦታዎች ላይ የሚጻፍ ነገር አይኖርም፡፡

## አንቀፅ 12. በመራጮች ምዝገባና ድምጽ መስጫ ቦታ መገኘት ስለሚችሉ ሰዎች

በመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ መስጫ ቦታ መገኘት የሚችሉትን ሰዎች በሚመለከት የመራጮች ምዝገባ እና የምርጫ፣ ድምጽ ቆጠራ እና ውጤት አገላለፅ መመሪያዎች ላይ የተደነገጉት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 13. በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያበቁ ሁኔታዎች

1. በአዋጁ መሠረት:-

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሆነች፣

ለ) በምዝገባው ዕለት እድሜዋ 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣

ሐ) ድምጿ በሚቆጠርበት የምርጫ ክልል ቢያንስ 6 ወር የኖረች፣

መ) ልዩ የምርጫ ጣቢያ በተቋቋመበት ተቋም ውስጥ የምትኖር ወታደር፣ ከፍተኛ ትምሕርት ተቋማት የምትማር ተማሪ፣ እንዲሁም በምርጫ ክልሉ ውስጥ የምትኖር ከመኖሪያ ቀዬዋ የተፈናቀለች ዜጋ ከሆነች በመራጭነት መመዝገብ ትችላለች፡፡

ሠ) ተቋሙ በሚገኝበት የምርጫ ክልል መደበኛ ነዋሪ የሆነ መራጭ በመደበኛ የምርጫ ጣቢያ መመዝገብ ስለሚችል በልዩ ምርጫ ጣቢያ መመዝገብ የለበትም፡፡

2. አንድ በልዩ የምርጫ ጣቢያ የተመዘገበ መራጭ ድምጽ የሚሰጠው በተመዘገበበት ልዩ የምርጫ ጣቢያ ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 14. በመራጭነት ለመመዝገብ የሚቀርቡ የማንነት መለያ ማስረጃዎች

1. ማንኛዋም ሰው በአዋጁ፣ በመራጮች ምዝገባ መመሪያ እንዲሁም ከላይ በአንቀጽ 13 በተቀመጠው መሠረት በልዩ ሁኔታ በሚቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎች በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያበቁ ሁኔታዎችን ማሟላቷን፣ ማንነቷን እና በመደበኛ የመኖሪያ ቦታዋ ነዋሪ መሆኗን በማረጋገጥ መመዝገብ ትችላለች፡፡
2. ማንኛውም ሰው ለመመዝገብ ስትቀርብ ማንኛውም ማንነቷን የሚያስረዳ ሰነድ እንዲሁም በመደበኛ የመኖሪያ ቦታዋ ነዋሪ መሆኗን የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ አለባት፡፡
3. ተመዝጋቢዋ ከመኖሪያ ቀዬዋ የተፈናቀለች ዜጋ ከሆነች አግባብ ባለው ባለስልጣን የተሰጣት ፎቶግራፍ ያለው ማንነቷን የሚገልጽ ሰነድ ተቀባይነት አለው፡፡
4. ተመዝጋቢዋ ሰነዶችን ማቅረብ ካልቻለች መዝጋቢዎች መራጯ የተቋሙ ነዋሪ መሆኗን ለይተው የሚያውቋት ከሆነና በተጨማሪ አንድ የተቋሙ የአስተዳደር ሰራተኛ ምስክርነት ወይም መራጯ በመደበኛ ትኖርበት ከነበረው ወረዳ ወይም ቀበሌ ለረጅም ጊዜ ነዋሪ መሆናቸው የተረጋገጠ ሁለት ግለሰቦች በሚሰጡት ምስክርነት መመዝገብ ትችላለች፡፡ በተጨማሪም መደበኛ ነዋሪነታቸው የተረጋገጡ በተቋሙ ውስጥ የሚኖሩ ሁለት ግለሰቦች በሚሰጡት ምስክርነት ማስረጃ አልባዋን ተመዝጋቢ ለመለየት ከተቻለ ሂደቱ ቦርዱ በሚያዘጋጀው በቃለ ጉባኤ ተይዞ ምዝገባው ሊከናወን ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የአገር ውስጥ ተፈናቃይ ተመዝጋቢ አብረዋት የተፈናቀሉ እና መደበኛ ነዋሪነታቸው የተረጋገጠ ሁለት ግለሰቦች በሚሰጡት ምስክርነት ልትመዘገብ ትችላለች፡፡ ሂደቱም አስፈፃሚዎች በሚፈርሙበት ቃለ ጉባዔ ላይ ይሰፍራል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ስር የተዘረዘሩት ማንነትን ለማረጋገጥ መቅረብ የሚገባቸውን ሰነዶች ወይም ምስክሮች ማቅረብ ያልቻለ አንድ ተፈናቃይ፣ ወደ ተፈናቃዮች ጣቢያ በሚገባበት ወቅት የጣቢያው አስተዳደር ያከናወነው ምዝገባ ካለ፣ የመዘገቡን ቅጂ በማቅረብ ማንነቱን ማረጋገጥና መመዝገብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 15. የመራጮች ምዝገባ ጊዜ

1. የመራጮች ምዝገባ ቦርዱ በይፋ በሚያወጣው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ይካሄዳል፡፡
2. ቦርዱ በአዋጁ መሠረት በልዩ ሁኔታ በሚቋቋም የምርጫ ጣቢያ የሚመርጡ መራጮች ከምርጫው ቀን ቀደም ብለው እንዲመዘገቡና ድምጽ እንዲሰጡ በመወሰን በምርጫ የጊዜ ሰሌዳው ውስጥ ሊያካትት ይችላል፡፡
3. በአዋጁና የመራጮችን ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት ቦርዱ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ በማጋጠሙ ምክንያት የምዝገባ ጊዜ ያለፈባት ሰው በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያስችላትን

መስፈርት የምታሟላ ከሆነ ቦርዱ በሚወስነው ልዩ የምዝገባ ቀን በልዩ ሁኔታ ልትመዘገብ ትችላለች፡፡

4. ቦርዱ በልዩ የምርጫ ጣቢያዎች ለሚያደረገው ምርጫ የመራጮች ምዝገባ የሚጀምርበትን ቀን ወስኖ በምርጫ ሰሌዳው በማካተት ምዝገባው ከመጀመሩ ከ15 ቀናት በፊት ለመራጮቹ ተደራሽ በሆኑ የመገናኛ ብዙሃን ወይም በሌሎች የማስታወቂያ መንገዶች አማካይነት ይገልፃል፡፡
5. የመራጮች ምዝገባ ቦርዱ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ቅዳሜ እና እሁድን ጨምሮ በሕግ የተደነገጉ የሕዝብ በዓላትን ሳይጨምር በመንግሥት የሥራ ሰዓት ይከናወናል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## <u>ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት እና የምርጫ አስፈፃሚዎች አሠራር</u>

### አንቀጽ 16. የልዩ ምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት እና አሰራር

1. የምርጫ ክልል እና የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በሚሰሩባቸው አካባቢ የተቋቋሙ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎችን የማስተዳደርና እንደአስፈላጊነቱ የማገዝም ሀላፊነት አለባቸው፡፡
2. በተቋሙ ውስጥ የሚቋቋሙ ልዩ የምርጫ ጣቢያዎች መሠረት የሚያደርጉት ከመላ ሃገሪቱ ወደተቋሙ የመጡ መራጮችን ብዛትና የመጡበትን ክልል ሲሆን፡-

   ሀ) አንድ ልዩ የምርጫ ጣቢያ ከ700 የማይበልጥ መራጭ እንዲኖረው ተደርጐ ይደራጃል።

   ለ) ከአንድ ክልል ወደየተቋሙ የመጡ መራጮች በየ700 ተመድበው አንድ የምርጫ ጣቢያ ይቋቋማል፤ የመራጮቹ ብዛት ከ700 በላይ እንደሚሆን የሚጠበቅ ከሆነ ተጨማሪ የልዩ የምርጫ ጣቢያዎችን ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡

   ሐ) ከአንድ ክልል ወደየተቋሙ የመጡ መራጮች ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ እንደሚሆን የሚጠበቅ ከሆነ ከሌላ ምርጫ ክልል ከመጡ አነስተኛ ቁጥር ካላቸው ጋር በጋራ አንድ ልዩ የምርጫ ጣቢያ እንዲቋቋም መደረግ ይኖርበታል፡፡

### አንቀጽ 17. የልዩ ምርጫ ጣቢያ ምርጫ አስፈጻሚዎች ተግባር እና ሀላፊነት

የልዩ ምርጫ ጣቢያ ምርጫ አስፈጻሚዎች የሚኖራቸውን ተግባርና ኃላፊነት በተመለከተ ቦርዱ ያወጣው የምርጫ አስፈጻሚዎች ተግባር እና ኃላፊነት መመሪያ እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል።

### አንቀጽ 18. መራጮች የመጡበትን ምርጫ ክልል እንዲያውቁ የሚሰጥ መረጃ

1. ቦርዱ ልዩ መራጮች የሚመዘገቡበትን ልዩ የምርጫ ጣቢያ እንዲያውቁ እንዲያግዝ የተለየ የህዝብ ማሳወቂያ ዘመቻ ያካሂዳል እንዲሁም ልዩ ምርጫ ጣቢያው በሚገኝበት ቦታ የመራጮች መረጃ ይሰጣል፡፡
2. ስለ ልዩ ምርጫ ጣቢያዎችን እንዲያውቁ መረጃ መስጠት እና የልዩ ጣቢያውን ስም በጉልህ መፃፍ ያስፈልጋል፡፡
3. ለምዝገባ ወደ ምርጫ ጣቢያው ሲመጡ የመጡበትን ክልል፣ ዞን፣ ምርጫ ክልል፣ ወረዳ እና ቀበሌ በሚገባ አውቀው እንዲመጡ ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡
4. በአዋጁ መሠረት ማንኛዋም መራጭ በአንድ ምርጫ ጣቢያ ከአንድ ጊዜ በላይ መመዝገብ ወይም በሌላ የምርጫ ጣቢያ ድጋሚ መመዝገብ እንደሌለባት ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

### አንቀጽ 19. የአመዘጋገብ ሂደት

1. ለአንድ ምርጫ ጣቢያ አንድ መዝገብ ይኖራል፡፡
2. ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት መራጮች በጥንቃቄ በየክልሉ፣ በየምርጫ ክልሉ፣ እንደአግባብነቱ በወረዳ እንዲሁም በጣቢያዎች ለይቶ የመመደብ ሥራ መከናወን ይኖርበታል፡፡
3. መራጮችን በየክልሉ እና በየምርጫ ክልሉ በጥንቃቄ ለይቶ መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 2 (መ) ስር እንደተገለጸው አንድ አይነት የምርጫ ክልሎች ላልሆኑ በወረዳቸው ለይቶ መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡
4. በአዋጁ አንቀጽ 22 መሠረት በልዩ ሁኔታ በሚቋቋመው የምርጫ ጣቢያ የምትመዘገበው መራጭ የተለዩ ሁኔታዎች የሚመዘገብበትን ዐምድ ጨምሮ መዝገቡ የሚጠይቀውን ማንኛውንም መረጃ ሞልቶ በተመሣሣይ መልኩ በመራጮች ምዝገባ ካርዱ ላይ መገልበጥ ይኖርበታል፡፡
5. የአንድ ድምጽ የሚቆጠርበት ምርጫ ክልል መደበኛ ነዋሪ የሆኑ መራጮች ራሱን በቻለ በአንድ መዝገብ መመዝገብ አለባቸው፡፡
6. ከተለያየ የምርጫ ክልሎች የመጡ መራጮች በአንድ ምርጫ ጣቢያ ሲስተናገዱ፣ የእያንዳንዱ የምርጫ ክልል መራጮች በተለያዩ የምርጫ መዝገቡ ገጾች ላይ ይመዘገባሉ፡፡
7. በምርጫ ሕጉ የተዘረዘሩት የመራጮች መዝገብ ይዘት እንደተጠበቀ ሆኖ በድምፅ መስጫ ቀን መራጩን በመዝገቡ ላይ በቀላሉ ለማግኘት እንዲያግዝ መዝጋቢዋ ትኩረት ሰጥታ በመዝገቡም ላይ ሆነ በካርዱ ላይ የሚሞሉ መረጃዎችን ማለትም የመራጭ መለያ ቁጥር፣ የገፅ ቁጥር፣ የመዝገብ ቁጥር እና ተራ ቁጥር በመራጮች ምዝገባ ካርድም ላይ ሆነ በመራጮች መዝገብ ላይ በተመሳሳይ በጥንቃቄ ማስፈር አለባት፡፡

### አንቀጽ 20. የመደበኛ መኖሪያ ቦታ የምርጫ ክልል በጥንቃቄ መለየት

አንድ መራጭ የመደበኛ መኖሪያ ቦታዋን የምርጫ ክልል በመዝገቡ እና በመራጭነት ምዝገባ ካርዷ ላይ ከማስመዝገቧ በፊት የሚከተሉትን መለየት አለባት፡፡

1. የመጣችበትን ክልል፣
2. የመጣችበትን ዞን፣
3. የመጣችበትን ወረዳ ወይም የከተማ መጠሪያ ስም እና
4. የመጣችበትን ቀበሌ፡፡

## አንቀጽ 21. የምዝገባ ሂደት ውጤት አሞላል

በቦርዱ የመራጮች ምዝገባ መመሪያ አንቀጽ 26 እና 27 የተደነገገው ቢኖርም፤ የምርጫ አስፈጻሚዋ የተመዝጋቢዋን ቁጥር ከመዝገቡ ላይ በየልዩ ምርጫ ጣቢያ በከፍተኛ ጥንቃቄ በመለየት ለዚህ በተዘጋጀው ቅፅ ላይ በመሙላት ተቋሙ ለሚገኝበት የአካባቢው ምርጫ ክልል ጽ/ቤት ሪፖርት ታደርጋለች፡፡

## አንቀፅ 22. የመራጮችን መዝገብ ለህዝብ ግልፅ ስለማድረግ

በቦርዱ የመራጮች ምዝገባ መመሪያ የመራጮችን መዝገብ ለሕዝብ ይፋ ስለማድረግ በሚደነግገው አግባብ የመራጮች ምዝገባ እንደተጠናቀቀ የመራጮች መዝገብ በተቋሙ በተቋቋመው በልዩ የምርጫ ጣቢያ ውስጥ ለተከታታይ 10 ቀናት ይፋ ወጥቶ ህዝብ በግልፅ እንዲያየው ይደረጋል።

## አንቀጽ 23. መዝገብ ስለመያዝ

የልዩ ምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የመራጮች ምዝገባ የተከናወነባቸው መዝገቦች ምዝገባው ሲጠናቀቅ በቃለ-ጉባዔ ከተያዘው ወይም በአዋጁና በቦርዱ የመራጮች ምዝገባ መመሪያ መሠረት በቦርዱ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከተመዘገበው የመጨረሻ ተመዝጋቢ መለያ ቁጥር ውጭ አዲስ ተመዝጋቢ ያልተመዘገበባቸው መሆኑን ለታዛቢዎችና ለእጩ ወኪሎች በግልፅ ካሳየ በኋላ የመዝገብ ሹሙ መዝገቡን ለአካባቢው የምርጫ ክልል ይሰጣል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የድምፅ አሰጣጥ ሂደት

## አንቀጽ 24. የልዩ ምርጫ ጣቢያ ምርጫ አስፈጻሚዎች ተጨማሪ ኃላፊነቶች

የቦርዱ የድምፅ አሰጣጥ፣ አቆጣጠርና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ የልዩ ምርጫ ጣቢያ ምርጫ አስፈፃሚዎች በዚህ ምዕራፍ የተመለከቱትን ይፈፅማሉ፡፡

## አንቀጽ 25. ለምርጫ ጣቢያው ድምፅ ሰጪዎች የሚሰጥ ገለፃ

1. የምርጫ ጣቢያው ምርጫ አስፈፃሚዎች ለተቋሙ ድምፅ ሰጪዎች በምርጫ ጣቢያው በግልጽ በሚታይ ቦታ በሚንጠለጠሉ ፖስተሮች አማካይነት ገለጻ እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡

2. ገለጻ የሚደረግበት ፖስተር፤

ሀ) የድምፅ መስጫው ቦታ፣

ለ) የድምፅ መስጫውን ቀን፣

ሐ) የምርጫ ጣቢያው የሚከፈትበትና የሚዘጋበትን ሰዓት፣

መ) መራጩ በድምፅ መስጫው ዕለት የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ይዞ መምጣት እንዳለበት፣

ሠ) የሚካሄደው የምርጫ ዓይነት እና የድምፅ መስጫ ወረቀት ዓይነት፣

ረ) አንድ መራጭ ለመጣችበት ምርጫ ክልል ለየምርጫው ዓይነት ለምን ያህል ዕጩ ድምፅ መስጠት እንደምትችል እና እንዴት ድምፅ መስጠት እንዳለባት፣

ሰ) የድምፅ አሰጣጡን፣ የድምፅ ቆጠራውንና ውጤት አገላለፅን አጠቃላይ ሂደት፣

ሸ) ወደምርጫ ጣቢያው ማስገባት የሚከለከሉ ነገሮችንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በዝርዝር ማካተት አለበት፡፡

3. በልዩ ምርጫ ጣቢያ ለሚመርጡ መራጮች ድምጽ የሚሰጧቸውን እጩዎች በሚመለከተ በምርጫ ጣቢያው አካባቢ የእጩዎችን ስም፣ የተወከሉበት የፖለቲካ ፓርቲ እና አስፈላጊ የሆኑ መራጃዎችን እንዲሁም ለክልል ምክር ቤት ለምን ያህል እጩ ድምጽ መስጠት እንዳለባቸው የሚገልጽ ሰንጠረዥ አስቀድሞ በማዘጋጀት እና በመለጠፍ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

### አንቀጽ 26. የልዩ ምርጫ ጣቢያ ዝግጅት

1. የድምፅ መስጫ ዕለት ከመድረሱ በፊት መራጩ ድምፅ የሚሰጥበት የምርጫ ጣቢያ ምቹና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ በምርጫ አስፈፃሚዎች መዘጋጀት አለበት፡፡

2. ከላይ የተጠቀሰው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የልዩ ምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች፡-

ሀ) ለመራጮች አስፈላጊውን መረጃ የሚሰጡ ቦርዱ የሚያሰራጫቸውን የሚለጠፉ ፖስተሮች፣

ለ) ለድምፅ ቆጠራው መብራት ባይኖር ወይም በተለያየ ምክንያት ቢቋረጥ እንደየአባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ሻማ፣ ኩራዝ፣ ፋኖስ ወይም ማሾ፣

ሐ) እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ድምፅ በሚስጥር የሚሰጥበት ቢያንስ ሦስት የሚስጥር ድምፅ መስጫ ቦታ፣

መ) የድምፅ መስጫ ሳጥን የሚቀመጥበትን ቦታ፣

ሠ) በድምፅ መስጫው አቅራቢያ ለመራጩ ስለድምፅ አሰጣጡ ገለፃ የሚሰጥበትን ቦታ፣

ረ) ተቀማጭ የእጩ ወኪሎችና የምርጫ ታዛቢዎች የሚቀመጡበትና የድምፅ አሰጣጡን ሂደት በግልፅ ለመመልከት የሚችሉበትን ቦታ፣

ሰ) የመዝገብ ሹሞች የመራጮች ማንነትን እና መዝገብ ለማረጋገጥ የሚቀመጡበት፣ የድምፅ መስጫ ወረቀት ለመራጩ የሚሰጥበትና መምረጥን የሚያረጋግጥ ቀለም የሚቀባበት ቦታ ተለይቶ በተገቢው ሁኔታ በቅድሚያ መዘጋጀቱን፣

ሸ) የልዩ ምርጫ ጣቢያ በድምጽ መስጫ ጊዜ ሰፋ ያለ ስፍራ እና በቂ ጠረጴዛዎች መኖሩን ያረጋግጣሉ፡፡

## አንቀጽ 27. የተከለከሉ ተግባራት

1. ማንኛውም ሰው በምርጫ ጣቢያው 500 ሜትር ዙሪያ መለስ ርቀት ውስጥ በስካር መንፈስ ውስጥ ሆኖ፣ የጦር መሣሪያ በመያዝ ወይም በሌላ በማናቸውም ፀጥታን በሚያደፈርስ አኳኋን መገኘት የለበትም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው የጦር መሣሪያ ክልከላ በካምፖች ውስጥ ለሚገኙ ወታደሮች በሚቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎችም ላይ በምርጫ ጣቢያው 200 ሜትር ዙሪያ ክልል ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
3. ድምጽ ካልሰጡ መራጮችና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 ከተዘረዘሩት ሰዎች ውጪ ማንኛዋም ሰው ያለፈቃድ ወደምርጫ ጣቢያው በመግባት ወይም በምርጫ ጣቢያው ክልል ውስጥም ሆነ ውጭ በመሆን የምርጫውን እንቅስቃሴ ማወክ ወይም ማደናቀፍ የለባትም፡፡

## አንቀጽ 28. የምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ቁጥጥር

1. ማንኛውም የምርጫ ሰነድ እና ቁሳቁስ ከአንዱ ምርጫ አስፈጻሚ ወደ ሌላው በሚተላለፍበት ጊዜ ቦርዱ የምርጫ ቁሳቁስ ስርጭት፣ ርክክብ እና ጥበቃን በሚመለከት ባወጣው መመሪያ መሠረት ሕጋዊ የርክክብ ስርዓትና ጊዜን ተከትሎ መፈፀም አለበት፡፡

2. ልዩ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ከአካባቢው ምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት እንደታሸጉ የተረከባቸውን ሰነዶችና ቁሳቁሶች ቀደም ሲል ታሽገው በነበረበት ሁኔታ እሽጉ ሳይፈታ መቆየቱን በመረካከቢያ ቅጹ ላይ የተመዘገቡትን የማሸጊያ ቁልፍ ቁጥሮች በማመሳከር ለተቋሙ የምርጫ ታዛቢዎችና ለተቀማጭ የእጩ ወኪሎች በግልፅ ታሳያለች፡፡

3. በመረካከቢያ ቅጹ ላይ የተመዘገበው ቁጥር በማሸጊያ ቁልፉ ላይ ካለው የተለየ ከሆነ ወይም የመረካከቢያ ቅጹ ተሰርዞና ተደልዞ ከሆነ ጉዳዩ በምርጫ አስፈጻሚዎችና በእጩ ተወካዮች በቦርዱ በተዘጋጀ ቃለ ጉባኤ ቅጽ ላይ ተመዝግቦ እሽጉ ተፈትቶ እንዲቆጠር ይደረጋል፡፡ የአካባቢው ምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት ስለ ሁኔታው ይነገረዋል፡፡

**አንቀጽ 29. ለድምፅ መስጫ ወረቀቶች ስለሚደረግ ጥንቃቄና ቁጥጥር**

ለድምጽ መስጫ ወረቀቶች የሚደረገው ጥንቃቄና ቁጥጥር በቦርዱ የድምጽ አሰጣጥ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ላይ በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 30. የድምፅ መስጫ ሳጥን እና የሳጥን ማሸጊያ ቁጥጥር**

ለድምጽ መስጫ ሳጥን እና የሳጥኑ የፕላስቲክ ማሸጊያ የሚደረገው ጥንቃቄና ቁጥጥር በቦርዱ የድምጽ አሰጣጥ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ላይ በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 31. የድምፅ መስጫ ሰዓት**

የድምጽ መስጫ ሰዓት በቦርዱ የድምጽ አሰጣጥ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ ላይ በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 32. የልዩ ምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች**

የልዩ ምርጫ ጣቢያ ምርጫ አስፈጻሚዎች በቦርዱ የድምጽ አሰጣጥ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ በተደነገገው መሰረት ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው፡፡

**አንቀጽ 33. የልዩ ምርጫ ጣቢያ የድምፅ አሠጣጥ ሂደት**

በአዋጁ ክፍል ሦስት ምዕራፍ አራት እንዲሁም በቦርዱ የድምጽ አሰጣጥ፣ አቆጣጠርና የውጤት አገላለጽ መመሪያ መሰረት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ በልዩ የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጡ ከዚህ በታች በተዘረዘረው መልኩ ይካሄዳል፡፡

የድምፅ መስጫ ወረቀት አዳይ፦

ሀ) የድምፅ መስጫ ወረቀት አዳዮች በልዩ ምርጫ ጣቢያው ያሉ የተመዘገቡ መራጮች በሚኖሩበት የምርጫ ክልሎች ይከፋፈላሉ።

ለ) እያንዳንዱ የድምጽ መስጫ ወረቀት አዳይ የመራጭ መለያ ካርዱን በመመልከት፤ መራጯ ለምትኖርበት የምርጫ ክልል መስጠት ያለባትን የድምጽ መስጫ ወረቀት በመለየትና፤ ጣቶቿ የማይለቅ ቀለም መቀባታቸውን በማረጋገጥ የድምፅ መስጫ ወረቀቱን ትሰጣታለች፡፡

ሐ) በተጨማሪም ለማንም በማያዳላ መልኩ የድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ እንዴት ምልክት ማድረግ እንዳለባት ታስረዳታለች፡፡

**አንቀጽ 34. የልዩ ምርጫ ጣቢያው የድምፅ ቆጠራ**

1. በምርጫ ሕጉ እንዲሁም በቦርዱ የድምጽ አሰጣጥ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ መመሪያ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩ የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ ቆጠራ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ይይዛል፦

ሀ) ድምጽ የሰጡ መራጮችን አጠቃላይ ብዛት እንዲሁም በእያንዳንዱ ምርጫ ክልል ድምጽ የሰጡ መራጮች ብዛት ይረጋገጣል፣

ለ) በድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ ያሉ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች አጠቃላይ ቁጥር እንዲሁም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በምርጫ ክልሎች ተለይተው ይቆጠራሉ፡፡

ሐ) የእያንዳንዱ የምርጫ ክልል የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በዕጩ ተወዳዳሪዎች ስር ተለይተው ይቆጠራሉ፡፡

2. በየምርጫ ጣቢያው በምርጫ ክልል ተለይቶ የተቆጠረው ድምፅ ተጠናቅሮ ለዚሁ በተዘጋጀው የምርጫ ክልል ማስተያያ እና ውጤት ማሳወቅያ ቅፅ ላይ ይሞላል፡፡ የማስተያያ እና ውጤት ማሳወቂያ ቅጽ እንዲሁም የድምፅ መስጫ ወረቀቶቹ በድምፅ መስጫ ሳጥን በምርጫ ክልሎች ተለይተው በፖስታ ታሽገው እና ውጤቱ ደግሞ ከተከፈተ በሚያስታውቅ ማሸጊያ ታሽጎ ወደ አካባቢው የምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት ወዲያውኑ ተጠብቀው እንዲላኩ ይደረጋል፡፡

3. የልዩ ምርጫ ጣቢያው የሚገኝበት የአካባቢው የምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት ውጤቱን ሳያዳምር ባለበት ሁኔታ ለቦርዱ ዋና ጽሕፈት ቤት ያስተላልፋል፡፡

**አንቀጽ 35. ስለአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አወቃቀርና ስለአቤቱታ አቀራረብ**

በልዩ የምርጫ ጣቢያው በሚከናወነው የምርጫ ሂደት ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች በየደረጃው በሚቋቋም አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀትና አሠራር መመሪያ መሠረት ይፈፀማል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀጽ 36. ስለመተባበር**

ማናቸውም የፌዴራልም ሆነ የክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የፖለቲካ ድርጅት፣ ቡድን፣ የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ ይህንን መመሪያ በሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት::

**አንቀጽ 37. የምርጫ ጣቢያው ደህንነት**

ማንኛውም የፖሊስ ወይም የፀጥታ አካል የልዩ ምርጫ ጣቢያውን ደህንነት በተመለከተ በምርጫ አስፈጻሚዎች የጥበቃ ጥያቄ ሲቀርብለት ልዩ የምርጫ ጣቢያውን፣ የምርጫ አስፈጻሚዎችን እንዲሁም ሰነድና ቁሳቁሱን በመጠበቅ ረገድ ጥበቃ የማድረግ፣ የመተባበር፣ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 38. ቦርዱ ስላወጣቸው መመሪያዎች ተፈፃሚነት**

በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተካተቱ እና ያልተሸፈኑ ጉዳዮች በአዋጁ እና ቦርዱ ባወጣቸው ሌሎች መመሪያዎች ይሸፈናሉ፡፡

**አንቀጽ 39. የተሻሩ መመሪያዎች እና አሠራሮች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

**አንቀጽ 40. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከፀደቀበት ከታህሳስ 11 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ብርቱካን ሚደቅሳ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ